# የጤና እና የደህንነት ፖሊሲ

ቀን ፡ ግንቦት 01 ፥ 2016

Allied Gold Corporation ("Allied" ወይም "ኩባንያው") የሁሉንም ሠራተኞች ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ እና ለማስተዋወቅ ቁርጠኛ ነው። ኩባንያው ሁሉም ጉዳቶች እና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች መከላከል የሚቻል እንደሆኑ ያምናል፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ትርፋማ ወርቅ በ "ዜሮ ጉዳት" መንፈስ ለማምረት ወስኗል። ይህንን ዓላማ ለማሳካት ኩባንያው በሁሉም የኩባንያው እንቅስቃሴዎች ላይ የሚተገበር የጤና እና የደህንነት ፖሊሲን ትርጓሜ እንደሚከተለው በማስቀመጥ በሥራ ላይ አውሏል።

ኩባንያው የሚከተሉትን ያደርጋል፡-

- የጤና እና የደህንነት ዕሳቤዎች በሁሉም የኩባንያው ገጽታዎች ውስጥ መካተታቸውን የሚያረጋግጥ የኩባንያ ባህልን ማስተዋወቅ።
- እንደ ዝቅተኛ መመዘኛ ተጠያቂ የምንሆንባቸውንና ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎች እና ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን ለማክበር።
- በኩባንያው አፈጻጸም ውስጥ ቀጣይነት ያለው መሻሻልን ለመደገፍ የአስተዳደር ሥርዓትን ለማዘጋጀት እና ለማስቀጠል።
- ለኩባንያው የጤና እና ደህንነት አፈጻጸም አመራርን እና ተጠያቂነትን ማሳደግ።
- የጤና እና ደህንነት ዓላማዎችን እና ዒላማዎችን ማዘጋጀት እና በመደበኛነት መገምገም።
- አደጋዎችን እና እድሎችን በንቃት በመለየት እና በመገምገም እነዚህን ሀሳቦች በሁሉም የቢዝነስ እቅድ ሂደት ውስጥ በአሰሳ፣ በልማት፣ በኦፕሬሽኖች እና ማዕድን ማውጫን በመዝጋት ሂደቶች ውስጥ ማዋሃድ ወይም ማካተት።
- በሁሉም የቢዝነስ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የጤና እና የደህንነት ስጋቶች እና ተጋላጭነቶች የሚጠበቁ፣ የተለዩ፣ የተገመገሙ እና ቁጥጥር ውስጥ የዋሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ውጤታማ እና ተግባራዊ የአደጋ መለያ እና የአደጋ ግምገማ ሂደት ላይ ትኩረት ማድረግ።
- PPEን እና በአስተማማኝ እና በብቃት ለመሥራት የሚያስችሉ መሳሪያዎችን ጨምሮ የሙያ ጤና እና ደህንነት ዓላማዎቻችንን ለማሟላት በቂ ሀብቶችን ማዘጋጀት።
- ሁሉም ሰራተኞች እና ተቋራጮች የየራሳቸውን ኃላፊነት እንዲገነዘቡ ለማድረግ እና ቀጣይነት ባለው ትምህርት እና ስልጠና እውቀታቸውን የሚያሳድጉባቸውን እድሎችን ለመስጠት።
- ሠራተኞች ለሙያ ጤና እና ደህንነት አፈጻጸም ኃላፊነት እና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ማበረታታት።
- ሠራተኞች እና ተቋራጮች ደህንነቱ ያልተጠበቀ ሥራን ያለመሥራት መብታቸውን እንዲጠቀሙበት ማበረታታት።
- በሰው ኃይላችን እና በተቀባይ ማህበረሰባችን ውስጥ አጠቃላይ ጤና እና ደህንነት የመጠበቂያ ፕሮግራሞችን ማስተዋወቅ እና ማቋቋም።
- የኩባንያ እና የሳይት ደረጃ የጤና እና የደህንነት አፈጻጸምን በመደበኛነት መገምገም።

- በጤና እና ደህንነት ጉዳዮች ላይ የሰው ኃይል ተሳትፎን በንቃት ማበረታታት።
- በኩባንያው እንቅስቃሴዎች ላይ አስተያየት ለመጠየቅ እና ለማካተት ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይትን ማዳበር።
- ውጤታማ የአደጋ ጊዜ ዝግጁነትን ማስቀጠል።

ይህ ፖሊሲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በAllied ቁጥጥር ስር ለሆነ ቢሮ ወይም ጣቢያ የሚሠሩ ሁሉም ሠራተኞች እንዲሁም በኩባንያው ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ያሉ ኮንትራክተሮች ይመለከታቸዋል።

ፒተር ማርሮን (Peter Marrone)
**ሊቀመንበር እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ**

ዳንኤል ሬሲን (Daniel Racine)
**ፕሬዚዳንት እና ዳይሬክተር**